# አል-ኢስላም መጽሄት በሐምሌ 25 / 2000 ዓ.ል
# ከዳኢ ሳዲቅ ሙሐመድ ጋር ያደረገዉ ቆይታ



አል -ኢስላምመጽሄት በሐምሌ 25 / 2000 ዓ.ል ከዳኢ ሳዲቅ ሙሐመድ ጋር ያደረገዉ ቆይታ

አል -ኢስላም፡- በአዉቶብስ መሄድ በጣም ትጠላለህ ይባላል እዉነት ነዉ?

ሳዲቅ፡- ከየት እንዳገኛችሁት ይገርማል፤በአዉቶቢስ መሄድ አልወድም፡፡በሁለት ምክኒያቶች አንደኛ መጋፋት በጣም እጠላለሁ ገንዘብ አጥሮኝ እራሱ የተወሰነ ርቀት በእግር ሄጄ በታክሲ እሄዳለሁ እንጂ በባስ አልሄድም ሌላዉ ምክኒያቴ አንድ ዘመዴ እቃ እንድገዛለት 15 ብር ሰጠታኝ በአዉቶቢስ ተሳፈርኩና ተዘረፍኩ ይህ ያሳደረዉ ተፅዕኖ ያለም ይመስለኛል፡፡

አል-ኢስላም፡- ሳዲቅ ትዉልድና እድገትህ የትነዉ? ስንት አስቆጠርክ?

ሳዲቅ፡- ጉንችሬ ከተማ ልዩ ስሙ ጢድ የሚባል ቦታ በ1971 መስከረም 25 ተወለድኩ፡፡ይህ ማለት እድሜዬ 29 ዓመት ከ9 ወር አከባቢ ማለትነዉ፡፡

አል -ኢስላም፡- ክትፎ በጣም ትወዳለህ እንዴ?በጣም ታዘወትራለህ ሲባል ሰማዉ?

ሳዲቅ፡- ክትፎ በጣም እወዳለሁ፡፡

አል -ኢስላም፡- ክትፎንአንስተንቆጬንመተዉህሊናምአይፈቅድም፡፡ከቆጬጋርምንያህልነህአምቦዉሓምጠላትህነዉይባላል፡፡ እንዴትነዉይሄ?

ሳዲቅ፡- አምቦ ዉሃና ቆጬ በጣም ነዉ የምጠላዉ፡፡ ይህንን ስላችሁ ጉራጌነቴ ጥርጣሬ ዉስጣ እንዳይከታችዉ፡፡የራሴ ምክንያት አለኝ፡፡ቆጬ ሲበላ በጣም ጠንካራ ምግብ ነዉ፡፡የሆቴሉን እንዳታዩት ገጠር ስሄድ ጠንካራና ወፍራም ቆጬ ነበር የምንበላዉ፡፡ በጣም ነበር የሚያስቸግረኝ፡፡ አምቦ ዉሃ ደግሞ ጋዙ አይስማማኝም፡፡ስለዚህ ነዉ ቆጬ መብላትና አምቦ ዉሃ መጠጣት የምጠላዉ፡፡

አል -ኢስላም፡- የሀይማኖቶች ንጽጽር ልዩ መለያህ ነዉ፡፡መነሻህ ምንድነዉ?

ሳዲቅ፡-ወደ ንፅፅር የገባሁት በ1987 ዓ.ል የዛሬ 13 ዓመት ነበር፡፡በሁለት መነሻዎች ምክኒያት፡፡ የመጀመሪያዉ ምክንያቴ ቤቴ ጅማ ሰፈር አካባቢ ነዉ አልፎ አልፎ ፀጋ ቁርስ ቤት ገብቼ እመገባለሁ፡፡ባለቤቶቹ ደግሞ ጴንጤዎች ናቸዉ፡፡ አስታዉሳለሁ አንድ ቀን እኔ ምግብ አዝዤ መጥቶልኝ ስበላ ከፊት ለፊቴ የነበረዉ ሰዉ አብቅቶ ወደ እኔ መጣና እየሱስ ጌታ ነዉ አለኝ፡፡እዉቀት ባይኖረኝም ‹ጌታ አይደለም፡፡› አልኩት ‹ኧረ የጌቶችም ጌታ!› አለኝ ‹‹ጌታ አይደለም ነብይ እንጂ›› ስለዉ ‹እየሱስማ የአለማቱ ጌታ ነዉ፡፡› ብሎኝ ‹ዱዓ› አደረገልኝና ጭንቅላቴን ዳብሶኝ ሄደ፡፡ምላሽ መስጠት ለምን አቃተኝ ብዬ በጣም ተናደድኩኝ፤፤በሌላ ቀን ኪታብ ያስቀራኝ የነበረዉ ዑስታዝ ተማም ኑረዲን ይባላል አስተማሪዬ ቤቱ እየቀራሁ እያለ በማስታወሻ ደብተሩ ላይ አንድ ጥቅስ ተመለከትኩ፡፡ “እኔ ከራሴ አንዳች ነገር ማድረግ አይቻለኝም፡፡እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነዉ፡፡የላከኝን ፍቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻም፡፡እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር ምስክሬ እዉነት አይደለም፡፡ ” ዩ.ወንጌል 5፤30-31 የሚል ጥቅስ፡፡እየሱስ የተናገረዉ ነዉ ተብሎ ነዉ የተቀመጠዉ፡፡በመፅሀፍ ቅዱስ ላይ እንዲህ የሚል ካለ ክርስቲያኑን በሙሉ ማስለም እችላለሁ ብዬ አሰብኩ፡፡ይህንን ጥቅስ ይዤ ነዉ የተነሳሁት፡፡

የተማም ማስታወሻ ወደ መፅሐፍ ቅዱስ ፀጋ ቁርስ ቤት ያጋጠመኝ ደግሞ ሃይማኖቴን እንዳዉቅ ረዱኝ፡፡ከዚያም መፅሐፍ ቅዱስ ገዝቼ ማንበብ ጀመርኩ፡፡አልሃምዱሊላሂ ከ13 ዓመት በኋላ ከእናንተ ጋር በእንግድነት ተገናኘሁ፡፡

አል -ኢስላም፡- በፊት ቤተ-ክርስቲያን ታዘወትር ነበር፡፡ለዉይይት ነዉ ወይስ ለማድመጥ?

ሳዲቅ፡- ቤተ-ክርስቲያን እሄድነበር፡፡ይበልጥ እሄድ የነበረዉ የፕሮቴስታንቶች ሙሉ ወንጌል ቤተክርስተያን ስብከት ለመከታተል ነበር፡፡ቅዳሜና እሁድ እየሄድኩ አዳምጥነበር፡፡ወደ ዉይይቱ የገባሁት በአየሱስ  ታሪክ ላይ የተመሰረተ ፊልም በመሰረተ-ክርስቶስ ቤተክርሰቲያን በነፃ ተጋብዘን ከክርስቲያን ጓደኞቼ ጋር ሄደን በመሀል ሙብራቱን አጠፍተዉ መስበክ ጀመሩ፡፡፡እኔም አንዳንድ ጥያቄዎችን ፊልሙን ተንተርሼ መጠየቅ ጀመርኩ፡፡ከዚ በኋላ የማስታዉሳቸዉ አራት ቤተክርስቲያናት ገብቼ ተወያይቻለሁ፡፡

አል -ኢስላም፡- ቤተክርስቲያን ዉስጥ የተለያ ያጋጠመህ ክስተት አለ?

ሳዲቅ፡- አንዴ መሀመድ የሚባል የመሰረት ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ዘበኛ ጋር ተገናኘዉ፡፡ሰዉየዉ ቀድሞ ሙስሊም የነበረ አሁን ካፊር ሆኖ እንደተቀየረ ሰምቼ ስለነበር ቀጥታ ወደሱ ሄጄ እየሱስ እዉን ፈጣሪ ነዉን? የሚለዉን መፅሀፍ ሰጥቼዉ አንብበህ ስትጨርስ እንወየየለን ብዬዉ ሄድኩ፡፡በሌላ ቀን በዚህ መፅሐፍ ዙሪያ ከመሀመድ ጋር እየተወያየን ሳለ አንድ ክርስቲያን ሌላዉን ጓደኛዉን ይዞ ምን መሰለህ ወንድሜ ሰዎች መሀመድን እንዴት እዳሳሳቱት ታዉቃለህ ይለዋል (እኔን ለመንካት ይመስላል)፡፡በዚህ ሰዓት በጣም ተናድጄ በምንድነዉ ያሳሳቱት ንገረኝ እስቲ ስለዉ እኔ ካንተ ጋር አልወያይም አለኝና ጠሎኝ ወደ ዉስጠ ገባ፡፡ሌላ ወጣት ከዉስጥ ወጣና ሳዲቅ አለኝ፡፡እንዴት እንዳወቀኝ ገርሞኛል፡፡ሳዲቅ አንድ አጋንንት ያለበት ሰዉ አምጣና አንተ በመሀመድ ስም እኔ ደግሞ በኢየሱስ ስም ማን እንደሚያወጣ እናያለን አለኝ፡፡እኔም በአላህ ስም እንጅ በመሀመድ ስም አጋንንት አይወጣም፡፡ይልቅ ጋኔን ያለበትን አንተ አምጣ ብዙዉን ጊዜ ከጋንንት ጋር የዚህ አይነት ተሞክሮ ያላችሁ እናንተ ስለሆናችዉ ይልቅ ጋኔን ያለበትን አምጣና አንተ ፀልይበት እኔ ደግሞ ልቅራለትና እንይ ስለዉ እርግጥ ልታወጣ ትችላለህ በእኔ ፊት ግን አታወጣም አለኝ፡፡አካሄዱም በጣም ስላናደደኝ አይደለም የምታወጣዉን ሰዉ ያንተንም ላዉጣልህ አልኩት፡፡በመሀል ከዉስጥ ዋናዉ ሰባኪ ወጣና ከዚህ ሰይጣን ጋር ተዉ አላቸዉ፡፡ማን ነዉ ሰይጣን? ሰይጣን ማለት የሚያስለፈልፍ ከሆነ እዛ ዉስጥ የሚጮህ ሰዉ ፈልግ፡፡ከፈለክ መድረክ ላይ እንነጋገር ስለዉ ለምን ወረዳ 24 ፖሊስ ደዉላቹሁ አትጠሩም ሲላቸዉ፡፡እኔም በእልህ የምታደርገዉን አያለዉ ብዬቁጭ አልኩ፡፡ያዉ ከጊዜ በኋላ ነዉ ትዕግስትና የዳዕዋ ሂክማ (ጥበብ) የተማርኩት፡፡

አል -ኢስላም፡- ከስንት ሰዎች ጋር ተወያይተሃል?

ሳዲቅ፡- ኢትዮጵያ ዉስጥ ከ1000 ሰዎች በላይ የተወያየሁ ይመስለኛል፡፡ሰዎቹን እንዲህ ሊያበዛቸዉ የቻለዉ በዚህ መስክ ላይ የተሰማራ ብዙ ሰዉ አለመኖሩ ነዉ የሚል እምነት አለኝ፡፡ሁሉም ለክርክር ሲጋበዝ የሚጠራዉ እኔኑ ስለሆነ ይመስለኛል፡፡በዚህ ላይ ሁሉም ሊያስብ ይገባዋል፡፡በግሌ እኔን መንገድ ላይ ከአምስት ሰዎች በላይ ይዘዉ የተከራከሩኝ የሉም፡፡

አል -ኢስላም፡- በእጅህ የሰለመ ሰው አለ?

ብዙ ሰዎች አጋጥመዉኛል፡፡ከዕነዚህም አንደኛዉ መቶ አለቃ ተሾመ ይባላል፡፡አንድ ሙስሊም እህታችንን አግብቶ አንቺም ሀይማኖትሽን ሳትተይ እኔም በሀይማኖቴ ተባብለዉ ይኖራሉ፡፡በኋላ የእሷ ወንድም በጣም ያሳስበዉና ለዉይይት ይጋብዘዋል እሱም ተቀበለ፡፡ፈጣሪ ልጅ አለዉ ብለህ ታምናለህ ወይ አልኩት፡፡እሱም እንዴት ልጅ ይኖረዋልአለኝ፡፡መፅሐፍ ቅዱስህ ግን አለዉይላል፡፡በመዝሙር 2፡7 ላይ እግዚአብሄርም አለኝ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድኩህ ይላል፡፡ስለዉ እንዴት አምላክ ልጅ ይኖረዋል ይሄ የአምላክ ቃል አይደለም፡፡ብሎኝ ወዲያዉ ሰለመ ሌላኛው ሁላችሁም የምታቁት አለማየሁ ነዉ መድረክ ላይ የሰለመዉ፡፡እንዲሁም ሌሎችም፡፡

አል -ኢስላም፡- የተወያየሀቸዉ ሁሉ ለምን አይሰልሙም?

ሳዲቅ፡- ችግሩ ምን መሰለህ በዉይይት ሰዓት የሰዉ አለመሸነፍ ዉስጣዊ ስሜትና ማፈር ስለሚኖር ቀጥታ ሰልመዉ አታገኝም፡፡በኋላ ግን እከሌ ሰለመ ሲባል እሰማለሁ፡፡ከተወያዮች ሌላ አድማጮች ሲሰልሙ ግን ብዙ ጊዜ ያጋጥመኛል፡፡ በተለይ ኦሮሚያ ክልል ዉስጥ በአንድ ቀን 30, 40, 50 እየሆኑ መጥተዉ ሸሀዳ ያደረጉ ሰዎችን አይነት በህይወቴ አይቼ አላዉቅም፡፡

አል -ኢስላም፡- አለም አቀፍ የዳዕዋ ተሳትፎህ እንዴት ነዉ?ብታገኘዉ የምትመኘዉ ዳዒስ ማነዉ?

ሳዲቅ፡- አለም አቀፍ የዳዕዋ እንቅስቃሴ ላይ ምንም ተሳትፎ የለኝም፡፡እንኳን አለም አቀፍ መቼ አገር ዉስጥስ አዳረስን? እቅስቃሴ የማደርገዉም በግሌ ስለሆነ ለዚህ የሚጋብዘኝን ሁኔታ አላገኘሁም፡፡ሌላዉ ላግኘዉ ብዬ በጣም የተመኘሁት ዳዒ አላህይዘንላቸውና አህመድ ዲዳት ነበሩ፡፡ለዚህ ዳዕዋ ሞዴል ነበሩ፡፡

አል -ኢስላም፡- ሳዲቅ ባለቤቱን ያገባት ልዩ ዱአ አድርጎ ነዉ እንዴ?

ሳዲቅ፡- በተለየ ዱአ ሳይሆን የተለየ ኒያ ነበረኝ፡፡የምመኛትን ልጅ አላህ እንዲወፍቀኝ ኒያም ነበረኝ፡፡አላህ አሳካልኝና እኔም በጣም የምወዳትን ነጂሚያን ሰጠኝ፡፡አላህን ሁሌም አመሰግነዋለሁ፡፡

አል -ኢስላም፡- ሀይስኩል እያለህ ቁጥር ትወድ ነበር፡፡ከሂሳብ ጋር ቅርበትህ እንዴት ነዉ? ትምህርትስ የት አቆምክ?

ሳዲቅ፡- በህይወቴ ለአእምሮ ፈታኝ የሆነ ነገር እወዳለዉ፡፡ለምን? እንዴት? ወዴት? የሚሉ ጥቄዎችን መጠየቅም መመለስም ደስ ይለኛል፡፡ቤቴ ከ600 በላይ ኪታቦች (መጽሐፍት) አሉኝ፡፡አብዛኞቹ አነዚህንም ጥያቄዎች የሚመልሱ ዐቂዳ ነክ፣አስማእ ወሲፋት፣ጥያቄዎችን የሚመልሱ ናቸዉ፡፡የሚጠይቁ መፅሐፍትን ማገበብ ያስደስተኛል፡፡ፈታኝ ጥያቄዎችን ተጠየቄ ካልመለስኩ ይጨንቀኛል

አል -ኢስላም፡- የትምህርቱስ ነገር?

ሳዲቅ፡- ትምህርት 11ኛ ክፍል ልመዘገብ ስል የት/ቤቱ ዩኒት መሪ አቶ ፋሲል አይሃለዉ የሚባል ሰዉ ከዉስጡ በነበረ ጥላቻ ፂሜን እንድላጭ ካልሆነ ግን እንደማልመዘገብ ነገረኝ፡፡ለምን ስለዉ በቃ የትምህርት ቤቱ ህግና ደንብ ነዉ አለኝና ወላጅ እንዳመጣ ነገረኝ፡፡እንግዲህ አባቴ የሚያውቁኝ ጥሩ ተማሪ ሆኜ ስለነበረ በጣምተረበሹ፡፡ወደ ት/ቤት ይዣቸዉ ሄጄ እንዳልማር የተከለከልኩት ፂሜን ስላልተላጨሁ እንደሆነ ነገራቸዉ፡፡እኔም በአባቴ ፊት በዚህ የሙብረቅ ቅፅበት ፂሜ እግሬ ጫፍ ቁርጭምጨሚቴጋ ቢደርስ እንኳ እንደቀበቶ ወደኋላ አስረዋለሁ እንጂ አልነካዉም አልኳቸዉ፡፡አባቴም ጣልቃ ገብተዉ ፂምን መላጨት በሀይማኖታችን የተከለከለ ነዉ በህጋችሁ ከሌለ ለምን አይማርም አሉ፡፡በህጋችን አለ አቶ ፋሲል ና ላሳይህ ብሎኝ ወደ ቢሮ ሄድን፡፡መንገድ ላይ እያንዳንዱ ተማሪ የት/ቤቱን ህግና ደንብ የማክበር ግዴታ አለበት ሲለኝ ትክክል ነህ በህገ-ደንቡ ዉስጥ ግን ፂምን ማሳደግ ክልክል ነዉ የሚለዉን ማየት እፈልጋለዉ አልኩት፡፡በዚህ ሰዓት እንዲያውም አላሳይህም በቃ ብሎኝ ወደ ጉልበት ሄደ፡፡እኔ ደግሞ አቅምም ስለሌለኝ ወደ በላይ አካል አቤት አልኩ ዞን 5 ትምህርት መምሪያ ሄጄ ለዋና አዛገፉ ትምህርቴ በሰዎች ተጽእኖ እንደተስተጓጎለ ነገርኩት፡፡የመመዝገቢያ ጊዜዉ አለፈና ይህ አመት እንዲህ በከንቱ ተቃጠለ፡፡መማር ሳልችል አለፈኝ፡፡በቀጣዩ አመት ሌላ ትምህርት ቤት አንድመዘገብ መሸኛ ስጠይቃቸዉ የተሟላ መረጃ ስላልሰጡኝ እንደገና ከ10 መጀመር ግድ ሆነብኝና ጀመርኩ፡፡የዚያን ጊዜ እንዴት አይነት የሙብት ረገጣ እንደነበረ ሳስብ የገርመኛል፡፡ያቃጠልኩትን ጊዜ አሰብኩ ወደፊት ብቀጥል እንኳ የማመጣዉን ለዉጥ እና ለህዝብ መጥቀም መቻሌ አጠራጠረኝ፡፡ከዚያ ትምህርት ላይ ያለኝን ተስፋና ፍላጎት አየቀነስኩ ወደ ዳዕዋዉ ገባሁና ይበልጥ ንፅፅሩን ገፋሁበት፡፡አልሀምዱሊላህ ደስተኛ ነኝ፡፡

**አል -ኢስላም፡- ሂፍዝ ላይ አላህ ይጨምርልህ፡፡ከቁርዓን እና ከመፅሐፍ ቅዱስ ይበልጥ በቃል ያጠናኸዉ የትኛዉን ነዉ?**

ሳዲቅ፡- አላህ የሂፍዝ ችሎታን ሰጥቶኛል አልሃምዱሊላህ፡፡አንድን ጥቅስ በቃሌ መያዝ አለብኝ ብዬ ካመንኩበት እይዘዋለሁ፡፡ይበልጥ የትኛዉን በቃልህ ይዘህል የሚለዉ ግን ተገቢ ጥያቄ አይመስለኝም፡፡ቁርአንን አላህ በጣም አግርቶታል፡፡በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ቁርዓንን በቃላቸዉ አጥንተዋል፡፡ቁርአንን ለመያዝ በጣም ቀላል ነዉና፡፡የአስር አመት ልጅ የአፍ መፍቻ ቋንቋዉ ሌላ ሆኖ በቃሉ ሲያጠና ታያለህ፡፡ይህ የአላህም እገዛ ስላለበት ነዉ፡፡መፅሐፍ ቅዱስን ግን ከሌሎች ሠዎች በተሻለ በቃል ይዣለሁ፡፡በሁለት ምክንያቶች አንደኛዉ ለዳዕዋ ይጠቅመኛል ብዬ ስለማምንበትና ያመንኩበትን ነገር በትንሽ ጥረት መያዝ ስለምችል ነዉ፡፡ሌላዉ ደግሞ ተደጋጋሚ ዉይይቶችን ከተለያዩ የእምነት ተከታዮች ጋር ሳደርግ ተመሳሳይ ጥቅሶችን ስለምጠቀም ይያዝልኛል፡፡ለምሳሌ በዩሃንስ ወንጌል 5፡30 ላይ “እኔ ከራሴ አንዳች ነገር ማድረግ አልችልም፡፡” የሚለዉን ጥቅስ ስለ እየሱስ ስወያይ በተደጋጋሚ ስለምጠቀመዉ በቃሌ እይዘዋለሁ፡፡መፅሃፍ ቅዱስ መያዝ የጥረት ጉዳይ ሲሆን ቁርአን ግን የአላህ ቃልኪዳንም አለበት፡፡

**አል -ኢስላም፡- ሳዲቅ የአባትህ ስም ማን ነዉ? መጠሪያዉን ትወደዋለህ?**

ሳዲቅ፡- የአባቴ ስም መሀመድ ነው(ፈገግታ)፡፡ብዙ ሰዎች በስም ተመሳሳይ የሆነ ሰዉ ሲያጋጥማቸዉ ለመለየት ሳዲቅ መፅሐፍ ቅዱስ ይላሉ፡፡ለምልክት ተገደዉ ስለሚጠቀሙት ምንም አይመስለኝም፡፡እከሌ አይነ ስዉሩ ብሎ መጥራት በሸሪአችን አይፈቀድም፡፡አማራጭ ካጣህ ግን ስያሜውን ብትጠቀም አትከለከልም፡፡ለእኔ እያሾፉ አንዳንድ ወንድሞቻችን እንደሚያደርጉት ቅር ይለኛል፡፡በሌላ መንገድ ምልክት መስጠት ካልቻሉ ግን ችግር የለዉም፡፡ፈቅጃለሁ፡፡

**አል -ኢስላም፡- መጽሐፍ ቅዱስን ስታነብ በጣም የሚያስደስቱህና የሚገርሙህ የመፀሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች ንገረኝ፡፡**

ሳዲቅ፡- ሳነባቸዉ የሚያስደስቱኝ ብዙ ጥቅሶች አሉ፡፡ይበልጥ የሚያስደስትህ ካልከኝ የዩሀንስን ወንጌል 17፡3 ነዉ፡፡የ1954 እትም ላይ “የዘላለም ህይወትም እዉነተኛ አምላክ ብቻ የሆንከዉ አንተንና የላከዉን እየሱስ ክርሰቶስን ማወቅ ነዉ” ይላል፡፡ ይህ ማለትኮ “ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም ብሎ የመሰከረ … ኢሳ የአላህ ባሪያና መልዕክተኛዉ ነዉ ያለ… ጀነት ገባ” ከሚለዉ የኢስላም አስተምህሮ ጋር አንድ ነዉ፡፡አኛም ወደዚሁ ነዉ የምንጠራቸዉ፡፡ይህ ጥቅስ በቃ ዲኔ ላይ እንድፀና ያደርገኛል፡፡በጣም የሚገርሙኝ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች እጅግ በርካታ ናቸዉ፡፡ካለዉ የቦታ ጥበት አንጻር ግን ሶስት ብቻ ልንገርህ። አንደኛው ከእግዚአብሔር አምላክነት አንፃር እንዴት ይህንን ባህሪ ይላበሳል? ብዬ ሁሌም የምገረምበትና ክርስቲያኖች እንዲመልሱልኝ የምፈልገዉ ጥቅስ ነዉ ትንቢ ኢሳያስም 7፡20 ላይ “በዚያም ቀን እግዚአብሔር ከወንዙ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሦር ንጉሥ የራሱንና የእግሩን ጠጕር ይላጨዋል ምላጩም ጢሙን ደግሞ ይበላል።” ይላል፡፡ይህ የአምላክ ባህሪይ ነዉን? እንዴት እግዚአብሄር አምላክ ሆኖ ምላጭ ይከራያል? በጣም ግራ ነዉ የሚገባኝ፡፡ሁለተኛዉ ከሴት መብት አንፃር መፅሀፍ ቅዱስ ያለዉ እሳቤ ነዉ፡፡ኦሪት ዘሌላዋዉያን 15፡19-22 ላይ የወር አበባ ላይ ያለች ሴት የመብት ጥያቄ የሚመልስበት መንገድ ነዉ፡፡ “ሴት ፈሳሽ ነገር ቢኖርባት በሥጋዋም ያለው ፈሳሽ ነገር ደም ቢሆን፥በመርገምዋ ሰባት ቀን ትቀመጣለች የሚነካትም ሁሉ እስከማታ ድረስ ርኩስ ነዉ” ይላል፡፡የአረብኛዉ መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ሰባት ቀን ነጂስ ትሆናለች ይላል፡፡እርኩስ ነች የሚነካትም ሁሉ እስከማታ ድረስ እርኩስ ነዉ፡፡” አካለዊ ንክኪ እንዴት ያረክሳል? እሷ የምትቀመጥበት ነገር ሁሉ እርኩስ ነዉ የምትተኛበት ነገር ሁሉ እርኩስ ነዉ መኝታዋን የነካ ልብሱን ያጥባል፡፡” በእጁ እኮ ነዉ የነካዉ “ሰዉነቱን ይታጠባል፡፡ታጥቦም አልወረደለትም፡፡እስኪመሽ ይረክሳል፡፡” ለምንድነዉ ታዲያ መታጠብ ያስፈለገዉ? ባለትዳር ከሆነ እንዴት ከሚስቱ ጋርስ ይኑር? ሰላምታ ከተከለከለ እንዴት ይሁን? ለምሳሌ ባለቤትህን ከስራ አምሽተህ ስትገባ ላትስማት ነዉ ማለት ነዉ? አስቴርዮ መቼም ሙስሊም ስለማትሆን ከድጃ አልልም አስቀድሞ እንዲህ አይነት ነገር ስለሌለ ውሃ ስጭኝ ብለሀት የምትጠጣበትን ብርጭቆ ብታቀብልህ ብርጭቆዉም ሊረክስ ማለት ነዉ? ይህ ከሰዉ አእምሮዉ ሊሄድ የሚችል ህግ ነዉ? ሴቶችንም ይጨቁናል፡፡ይህ ጥቅስ ይቀጥልና “ከርሷ ጋር ግን አብሮ የተኛ እሱም እንደሷ 7 ቀን ይረክሳል፡፡” ይላል፡፡ሰዎች ይህንን ጥቀስ አንብበዉ ኢስላም ይጨቁናል ሲሉ በጣም ይገርማል፡፡ሰለሴቶች

መብት ይበልጥ ማንበብ የሚፈልግ ወንድም አህመዲን ጀበልን የሴት መብትና እኩልነት በኢስላምና በክርስትና ንፅፅራዊ አቀራረብ የሚለዉን መፅሀፍ ማንበብ ይችላል፡፡

ሦስተኛዉ አግራሞት የሚፈጥርብኝ ለነብያቶች የሚሰጠዉ የክብር ደረጃ ነዉ፡፡መቼም እኛ ሙስሊሞች ለነብያቶች አላህ ዘንድ ከሰዎች በላይ ከፍተኛ ክብር እንዳላቸዉ እናምናለን፡፡ጥቃቅን ጥፋቶች እንጂ ታላላቅ ወንጀሎች አይፈፅሙም፡፡ለሰዎች ሞዴልና መምህር ስለሆኑ አላህ ይጠብቃቸዋል፡፡መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በዘፍጥረት 19:30-38

**ሎጥም ከዞዓር ወጣ በዞዓር ይቀመጥ ዘንድ ስለ ፈራም ከሁለቱ ሴቶች ልጆቹ ጋር በተራራ ተቀመጠ በዋሻም ከሁለቱ ሴቶች ልጆቹ ጋር ተቀመጠ።**

ታላቂቱም ታናሺቱን አለቻት። አባታችን ሸመገለ፥ በምድርም ሁሉ እንዳለው ልማድ ሊገናኘን የሚችል ሰው ከምድር ላይ የለም

ነዪ አባታቻንንም የወይን ጠጅ እናጠጣውና ከእርሱ ጋር እንተኛ፥ ከአባታችንም ዘር እናስቀር።

በዚያችም ሌሊት አባታቸውን የወይን ጠጅ አጠጡት ታላቂቱም ገባች፥ ከአባትዋም ጋር ተኛች እርሱም ስትተኛና ስትነሣ አላወቀም።

በነጋውም ታላቂቱ ታናሺቱን አለቻት፡- እነሆ ትናንት ከአባቴ ጋር ተኛሁ ዛሬ ሌሊት ደግሞ የወይን ጠጅ እናጠጣው አንቺም ግቢና ከእርሱ ጋር ተኚ፥ ከአባታችንም ዘር እናስቀር።

አባታቸውንም በዚያች ሌሊት ደግሞ የወይን ጠጅ አጠጡት ታናሺቱም ገብታ ከእርሱ ጋር ተኛች እርሱም ስትተኛና ስትነሣ አላወቀም።

የሎጥም ሁለቱ ሴቶች ልጆች ከአባታቸው ፀነሱ።

ታላቂቱም ወንድ ልጅ ወለደች ስሙንም ሞዓብ ብላ ጠራችው እርሱም እስከ ዛሬ የሞዓባውያን አባት ነው።

ታናሺቱም ደግሞ ወንድ ልጅ ወለደች ስሙንም፡- የወገኔ ልጅ ስትል አሞን ብላ ጠራችው እርሱም እስከ ዛሬ የአሞናውያን አባት ነው። ቢያንስ ሶስት ነገሮች ስላልገቡኝ መጠየቅ እፈልጋለሁ፡፡ ሰዉ መጠጥ ከጠጣና የሚደረግበትን ካላወቀ የዘር ፍሬን እንዴት ወደ መህጸን ሊያስተላልፍ ይችላል / ሁለተኛዉ ደግሞ እነዚህ ሴቶች የወለዷቸዉ ሁለት ወንዶችን ነዉ፡፡ ሞአብና አሞንን አላማዉ የሰዉ ዘርን ለመጠበቅ ከሆነ ሁለቱ ወንዶች ከማን ጋር ሊተኙ ልንል ነዉ / ከእናታቸዉ ጋር . ከዚህ ትዉልድ በኋላ ትዉልድስ እንዴት ተባዛ / በዝሙት ማለት ነዉ / አላህ ነብያትን ከእንደዚህ ፀያፍ ነገር የጠብቃቸዋል፡፡

አል-ኢስላም ፡- እስኪ ወጣቱን ምከረዉ

ሳዲቅ፡- ምክር በብዙ መልኩ ይታያል፡፡ እኔ ባለሁለት የዳዕዋ መስከም ይሁን በሌላ ያለዉን ወጣት አንድ ትልቅ ነገር መምከር እፈልጋለሁ፡፡ ወላሂ ዳዕዋ ላይ ባሳለፍኳቸዉ 10 ዓመታት ዉስጥ ትልቁን ልዩነት ያየሁት በእዉቀትና ጅህና መካከል ያለዉን ሰፊ ልዩነት ነዉ፡፡ እከሊት ከፈረች እከሌ ፕሮቴስታንት ሆነ ተብሎ ወደተወራበት ቦት ስሄድ ቀድሞ ነገር ስለእስለምና አንድ ነገር አያዉቁም፡፡ አላህንና ነብዩን ለይቶ ማየት የማይችሉ ሰዎች ናቸዉ ሲከፍሩ የሚታየዉ፡፡ እስልምና እንደሚያስተምረን እዉቀትና ድንቁርና ብርሃንና ጨለማ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዱ ሙስሊም ወጣት ሀይማኖቱን አብጠርጥሮ ሊያዉቅ ይገባል፡፡ ካፊሩ ዛሬ ስለኢስላም ትንሽ ያዉቅና ቁርአንን እንደፈለገ እየተረጎመ ሙስሊሙን ወደ ኩፍር ሲጠራ እናያለን፡፡ ምንመ ያለተበረዘና የሰዉ ልጅ እጅ ያለነካዉን ቁርአን ይዘን ግን ወደ ኢስላም መጠራት አቅናል፡፡ እዲያዉም ሰዎች ሁለት ቃል አረብኛ ስለተናገሩ ዲናችንን በጣም ያወቁ የመስለንና እንሸወዳለን፡፡ በኢስላም ላይ የሚወጡ አብዛኞቹ መፅሐፍትና መፅሄቶች ተራ አሉባልታና ወሬዎች ጠርቅም ናቸዉ፡፡ ስለዚህ ወጣቱ እስልምናን ሊያዉቅ ይገባል፡፡ ከድኛና ሙሀመድን ለመጠበቅ ያለን መሳሪያ እዉቀት ነዉ፡፡ እዉቀት ኖሮን በመረጃ ተደግፈን እህት ወንድሞቻችንን ከኩፍር ጨለማ እንጠብቅ፡፡ ሌሎችን ወደዲነል ኢስላም እንጥራ፡፡ “ከባሮቹ አላህን የሚፈረት የሚያዉቁት ብቻ ናቸዉ፡፡”

አል-ኢስላም፡- ሳዲቅ ብዙዎች ሁሌም የሚነሱት አንድ ጠያቄ አለ፡፡አንተን የተካህ ሰዉ አለ? ምኞትህስ ምንድነዉ?

ሳዲቅ፡- እንዳልከው ይህ የብዙ ሰዎች ጠያቄ ነዉ፡፡መንፈሳዊ ተቋም(theology collage)ኖሮን ስርአቱን ጠብቆ እንደሌሎች የምናስመርቅበት ኮሌጅ ቢኖረን ትልቅ ምኞቴ ነዉ፡፡እኔ እስከማዉቀዉ የሙስሊሞች አንድም ሀይማኖታዊ ተቋም አለመኖር በጣም ያሳፍራል፡፡ ቅድም እንዳልኩህ እኔ ዳዕዋዉን የማካሂደዉ በግሌ ነዉ፡፡የሚፈልገዉን ዉጤት ባያመጣም አንድ ሰዉ ማድረግ የሚችለዉን እያደረኩ ነዉ፡፡የሌሎች እገዛ ኖረዉም  አልኖረውም ያለኩህ ምኞቴ ተሳካም አልተሳካም ህግን ጠብቄ በህይወት እስካለዉ ድረስ ዳዓዋውን እገፋበታለሁ፡፡በግል በየመስጊዱ ሳስተምር እኔን ይተካሉ ብዬ የማስባቸዉ ሰዎችአሉ፡፡ወንድም አብዲ ቁርአንና መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በቂ እዉቀት አለዉ፡፡ እኔን ተክቶ ማስተምር ይችላል፡፡ ወደፊትም ጥሩ ደረጃ ላይ ይደርሳሉ ብዬ ተስፋ የማደርግባቸዉ ወንድሞች አሉኝ፡፡ለዳዕዋዉ ጥንካሬ ግን ሁሉም ሙስሊም የጋራ ሃላፊነት እንዳለበት በዚህ አጋጣሚ ለማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡፡

አል-ኢስላም፡- ከአንተ በቀጣይ ምን እንጠብቅ? ለሙስሊሙ ምን የደረሰ ስራ አለህ?

ሳዲቅ፡- ይህንን ዳዕዋ ይበልጥ ማስፋት እፈልጋለሁ፡፡በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ተጠቅሜ ዳዕዋዉን ማድረስ እፈልጋለሁ፡፡ሌላዉ ለእኔ ብዙም የማይመቸኝና ኢስላምምየ ማይፈልገዉ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ተራ አሉባልታዎችን ሀሰት መሆናቸዉን ለመግለጸ ምላሽ ለመስጠትም እሞክራለሁ፡፡በኡስታዛችን ዶ/ር ዛኪር ናይክ ላይ ለተነዛዉ አሉባልታ እንዳደረኩት ማለት ነዉ ዱዓ አድርጉልኝ፡፡ሁሉም በያለበት መስከ እስልምናን ያስፋፋ፡፡ዲኑን ለማያዉቁት ያድርስ፡፡ እስልምና ምልዑነት ለሰዎችያስተምር፡፡ የተዛባ እሳቤ ያላቸዉን ሰዎችንም ለማስተካከል ይሞክር፡፡ወዳጁን ከጠላቱ ይለይ፡፡ የእናንተም መፅሄት ስራ አንዱ የዳዕዋ መስከ ነዉ፡፡አላህ ያበርታችሁና ግፉበት፡፡እኔም ነገሮች ከተመቻቹልኝ ከእናንተ ጋር አብሬ ለመስራትና አምደኛ ሆኜ ለመቀጠል አስቤያለሁ፡፡

አል-ኢስላም፡- ሰዎች ያስፈራሩሃል ይባላል እንዴት ነዉ?

ሳዲቅ፡- ደግሞ ማነዉ የሚያስፈራራኝ? ይፍሩን እንጂ አንፈራቸዉም (በያዝነዉ እዉነት ምክንያት) አካለዊ ጉዳት ለማድረስ ከሆነ አልሀምዱሊላሂ እስካሁን ምንም ጉዳት አልደረሰብኝም፡፡ይህንን ለመፈጸም የሞከረም የለም፡፡ወደፊትም እርሱ ከሻዉ በቀር ምንም ሊደርስብኝ አይችልም፡፡ባይሆን ሙስሊሞች እዉነተኛ እና ታሪካዊ ጠላታችን አዉቀን ይህንን ይህን ጠላት ለመታገል ሁላችንም እንተባበር፡፡ጊዜዉ የመንቃት እንጂ የእንቅልፍ ዘመን አይደለምና፡፡

አል-ኢስላም፡- የሳዲቅ ዳዕዋ እንቅስቃሴ ከዲን አንጻር መሰረት የለዉም ይባላል፡፡ምን ምላሽ አለህ?

ሳዲቅ፡- ቅድሚያ መሰረት የለዉም የሚሉ ሰዎች ምን ማስረጃ እንዳላቸዉ ባዉቅ ደስ ይለኝ ነበር፡፡አላህ ግን በቅዱስ ቃሉ በሱረቱ-አልዒምራን 93 ላይነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) የያዕቁብ (ዐ.ሰ) ታሞ በነበረ ሰአት በራሱ ላይ እርም ያደረገውን ምግብ ምን እንደነበረ ተጠይቀው ሲመልሱ አይሁዶችም አስተባበሉ፡፡ኢስላምን የተቀበለዉ ስመ-ጥር የአይሁድ ሊቅ አብደላህ ኢብን ሰላም(ረ.ዐ) በቦታዉ ነበርና፡- ዋሻችሁ ተዉራትን አምጡና አንብቡ እዉነተኞች ከሆናችሁ ሲላቸው አላህ ሀሳቡ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ከላይ የተጠቀሰዉን የቁርአን አንቀጽ በድጋፍነት አዉርዶለታል፡፡ስለዚህ እኛም በዐቂዳ እና በነብያት ጉዳይ ላይ የተዛባዉን አመለካከት ለሰዎች ለመግለጽ ከመጽሀፋቸዉ መጥቀስ እንችላለን ማለትነዉ፡፡ ነብዩም በሀዲሳቸዉ "ሀዲሡ ዐን ቢኢስራኢለ ወላሀረጅ" ከመጽሐፉ ሰዎችኪታብ አዉሩ ችግር የለዉም (ቁርአንና ሀዲስን እስካልተጋጨ ድረስ) ስላሉ መጠቀም እንችላለን፡፡አንደ ኢብኑ-ተይሚያ "አልጀዋቡ ሰሂህ ሊመንበደለ ዲነል መሲህ" ኢብኑ ሀዝም "አል-ፊሰል ፊል ሚለሊ ወልአህዋኢ ወኒሀል" ሌሎችም ዑለሞች በዚህ ዙሪያ ከላየ ተጠቀሰዉን አይነት ኪታብጽፈዋል፡፡እነዚህ ሰዎች መሰረት የላቸዉም ማለትነዉ?

አል-ኢስላም፡- ስለነበረን ቆይታ ምስጋና እናቀርባለን፡፡

ሳዲቅ- እኔም አመሰግናለዉ፡፡

# ሒዳያ ኢስላማዊ ማዕከል

**ጥቅምት 2010 ዓ.ል**

ምስጋና

- ጹሁፉን በቴሌግራም በኩል ለየሕያ ኢብኑ ኑህ ያቀበለውን ወንድማችንን በማዕከላችን ስም ከልብ እናመሰግናለን።